# 1ኛ የውጤት/ማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ የ4ኛ ክፍል የወላጅ መመሪያ

በ1ኛ ማርክ መስጫ ወቅት፣ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክሂሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- በግራጫ ቀለም የታዩት ክህሎት እና ጽንሰሐሳቦች ትምህርት ተሰጥቷል ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ አልተመዘገበም።

## ሂሳብ 4/5

### ቁጥሮችና ግብረቶች በአስሮሽ ቤት

- በባለ በርካታ-አሃዝ ሙሉ ቁጥር ላይ በአንድ ላይ ያለዉ አሃዝ የሚወክለው ከበስተቀኙ ያለውን ቦታ በ10 እጥፍ ነው።
- ቁጥሮችን፣ የቁጥር ስሞችን፣ እና የተስፋፋ ፎርም በመጠቀም ባለ በርካታ-አሃዞች ቁጥርን አንብብ(ቢ) እና ጻፍ(ፊ)።
- >፣ =፣ እና < ምስሎች በመጠቀም ሁለት ባለበርካታ-ኣሃዝ ቁጥሮች ማወዳደር።
- ባለ በርካታ-አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን ወደማንኛውም ቦታ ለማጠጋጋት የቦታ-ዋጋ ግምትን/እውቀትን መጠቀም።
- በመደበኛ ስልተ ቀመር/algorithm በመጠቀም ባለበርካታ-ኣሃዞች ሙሉ ቁጥሮችን ኣቀላጥፎ መደመርና መቀነስ።
- ሙሉ ቁጥርን እስከ አራት ዲጅቶች በአንድ-ዲጅት ቁጥር አባዛ/ዢ፣ እና ሁለት ባለ2-ዲጅት ቁጥሮችን አባዛ/አባዢ።
- የሙሉ ቁጥር የማካፈል ውጤት እና ቀሪዎችን እስከ 4-ዲጅት ተካፋዮች እና 1-ዲጅት አካፋዮች ፈልግ/ጊ።

### ስሌቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- የማባዛት እኩልነት ምልክትን እንደ ማወዳደሪያ (ለምሳሌ፡- 35 = 5 × 7 ማለት 35 አምስት ጊዜ 7 እንደሚሆን እና ሰባት ጊዜ 5 እንደሚሆን ተርጉም/ሚ።
- ዎርድ ፕሮብሌሞችን ለመፍታት አባዛ/ዢ ወይም አካፍል/ይ
- ባለ-በርካታ ደረጃ የቃል ፕሮብሌሞች ከሙሉ ቁጥሮች ጋር በኣራት ግብረቶች በመገልገል መፍታት፣ ቀሪዎች መተርጎም ያለባቸውን ፕሮብሌሞች ጨምሮ። ያልታወቀ(ቁ ) ቁጥር(ሮችን) በፊደላት በመተካት እኩልነት ምልክት በመጠቀም እነዚህን ፕሮብሌሞች አሳይ።

### መለካት እና የተመዘገበ መረጃ

- ለሂሳብ ፕሮብሌሞች እና በተጨባጩ - ዓለም ለሚታዩ አራት ማዕዘን ቅርጽ የስፋት እና የዙሪያ ቀመር ተጠቀም/ሚ።
- ርቀቶችን፣ የጊዜ ክፍተቶችን፣ የፈሳሽ መጠኖችን፣ የነገሮች ክምሮችን፣ እና ገንዘብን የሚያካትቱ፣ ቀላል ክፍልፋዮችን ወይም ዴሲማሎችን የሚያካትቱ ፕሮብሌሞችን ጨምሮ፣ የቃል ፕሮብሌሞችን ለመፍታት በኣራት ግብረቶች መጠቀም።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፡- ስነ ፅሁፍ

- አንድ ጽሑፍ በግልጽ ምን እንደሚል በሚገለፅበት ጊዜ እና ከጽሑፍ ሃሳቦች በሚወሰዱበት ጊዜ በጽሑፉ የሚገኙ ዝርዝሮችና ምሳሌዎችን መጥቀስ።
- ከአንድ ታሪክ ዝርዝር ውስጥ ጭብጡን/መልእክቱን መለየት/መወሰን።
- ከአንድ ታሪክ ዉስጥ ገጸ ባህርይን፣ ዝግጅት፣ ወይም ክስተት/ሁነትን፣ ከጽሁፉ በልዩ/ዝርዝሮች ላይ በማተኮር በጥልቀት አስረዳ/ጂ። የተለያዩ ታሪኮች የሚተረኩበትን ኣስተያየቶች፣ በመጀመርያ- እና በሶስተኛ-ወገን ትረካዎች ያሉ ልዩነቶችን ጨምሮ፣ ማወዳደርና ማነፃፀር።
- የተመሳሳይ ዘውጎች/ጭብጦች እና ርእሶች (ለምሳሌ፣ የጥሩ እና የመጥፎ ኣንፃራዊነት) ኣያያዝን በታሪኮች ውስጥ ማወዳደርና ማነፃፀር።
- ለ4ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆነን ስነ ፅሁፍ ማንበብና መገንዘብ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡- መረጃዊ

- ኣንድ ፅሁፍ በግልጽ ምን እንደሚል በሚገለፅበት ጊዜ እና ከፅሁፍ ሃሳቦች በሚወሰዱበት ጊዜ በፅሁፉ የሚገኙ ዝርዝሮችና ምሳሌዎችን መጥቀስ።
- የኣንድን ፅሁፍ ዋና ሃሳብ መወሰን እና በዝርዝሮች እንዴት እንደሚደገፍ ማብራራት፤ ፅሁፍን ማጠቃለል።
- አንድን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተነገረን ከዉነት ወይም ርዕሰ ጉዳይ ማነፃጸር እና ማወዳደር።
- ለ4ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጃያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።

### ቋንቋ፡- የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም

- (አንድ - ለ- አንድ፣ በቡድን፣ እና መምህር እየመራ) ከሌሎች ጓደኞች ጋር በ4ኛ ክፍል ጽሑፍ እና ርእሶች ላይ በህብረት በበርካታ ገቢራዊ የሆኑ ውይይቶች ላይ ተሳተፍ/ፊ።

## ጽሑፍ

### ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር ውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካዎችን መጻፍ።
- ተሞክሮዎችን እና ክውነቶችን ለማዳበር ወይም ለሁኔታዎች የገፀባህርያትን መልሶች ለማሳየት በውይይትና በገለፃ መጠቀም።
- ከተተረኩ ተሞክሮዎች ወይም ክውነቶች የሚከተል ኣንድ መደምደሚያ ማቅረብ።

### መረጃያዊ/ገላጭ

- ርእሱን በግልጽ በማስተዋወቅ በአንቀጾቹ እና በክፍሎቹ መካከል ተመሣሣይ/ግንኙነት ያላቸው ሀሳቦችን አጣምር/ሪ፤ የአቀራረብ/ይዞታን (ለምሳሌ፡- የአርእስት አፃፃፍ)፣ ማሳያ/ለማብራሪያ የሚያገለግል፣ እና መረዳትን ለማገዝ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ ልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎችን ጨምሮ።
- ርእሱን በሃቆች፣ ፍቺዎች፣ ጭብጥ ዝርዝሮች፣ በጥቅሶች፣ ወይም ከርእሱ ጋር በተያያዙ መረጃዎችና ምሳሌዎች ማዳበር እና ከቀረበው መረጃ ወይም ማስረጃ ጋር የተዛመደ ኣንድ ማጠቃለያ ኣረፍተሃሳብ ማቅረብ።

### ኣስተያየት

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች የኣመለካከት ኣጫጭር ድርሰቶች መፃፍ፣ እንድን ኣስተያየት በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ።
- አንድን ርእስ ወይም ፅሁፍ በጥራት ማስተዋወቅ፣ አስተያየት መሰንዘር፣ እናም የጸሐፊውን ዓላማ ለመደገፍ የተዛመዱ ሃሳቦች የሚመደቡበት ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- እድገቱና ኣደረጃጀቱ ለተግባር፣ ኣላማ፣ እና ለኣድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮች እና ከትልልቅ ሰዎች ድጋፍ እና መመሪያ እያገኘህ(ሽ) እንደአስፈላጊነቱ፣ በማቀድ፣ ክለሳ በማድረግ፣ እና ለህትመት በማዘጋጀት ጽሑፍ አዳብር(ሪ)፣ እና አጠናክር(ሪ)። ጽሁፍን ለማዘጋጀት እና ለማሳተም እንዲሁም ከሌሎች ጋር ለመገናኘት፣ ቢያንስ አንድ ነጠላ ገጽ ታይፕ በማድረግ ኪቦርድን በጥሩ ሁኔታ የመጠቀም ችሎታ ለማረጋገጥ ኢንተርኔትን ጨምሮ ቴክኖሎጂ ተጠቀም/ሚ።
- የአንድ ርእስን የተለያዩ ገፅታዎች በመመርመር እውቀትን የሚገነቡ ኣጫጭር የምርምር ፕሮጀክቶችን ማከናወን።
- በተራዘመ የጊዜ ገደቦች እና ኣጫጭር የጊዜ ገደቦች ወይም የተለያዩ በዲሲፕሊን-በተለዩ ተግባሮች፣ ኣላማዎች፣ እና ታዳሚዎች በተደጋጋሚ መፃፍ።

### የቋንቋ ጥቅም

- በአንድ ርእስ ወይም ጽሑፍ ሪፖርት ማድረግ፣ አንድ ታሪክ መንገር፣ ወይም አንድን ተሞክሮ በተደራጀ መንገድ መተረክ፣ ዋናዋና ሃሳቦችን ወይም ጭብጥ መልእክቶች ለመደገፍ በተገቢ ሃቆች፣ እና አስፈላጊ፣ ገላጭ ዝርዝሮች በመጠቀም፤ ተቀባይነት ባለው ፍጥነት በጥራት መናገር።
- በእፃፃፍ፣ ኣነጋገር፣ በምንባብ፣ ወይም በማዳመጥ በቋንቋ እውቀት እና በህጎቹ መጠቀም።

## ሳይንስ

### የህይወት ሳይንስ

- ቁስአካል በእፅዋት፣ በእንሥሳት፣ ብስባሽ፣ እና አካባቢ መካከል እንዴት እንደሚዘዋወር ሞዴል በማዘጋጀት አስረዳ/ጂ።
- እፅዋት ለእድገት የሚያስፈልጓቸውን ቁሳቁሶች በዋናነት የሚያገኟቸው ከኣየርና ከውሃ ነው የሚለውን ሙግት መደገፍ።

### ፊዚካል ሳይንስ

- በእንስሳት ምግብ ዉስጥ የሚገኘው ሃይል በኣንድ ወቅት ከፀሃይ እንደነበር ለመግለፅ በሞዴሎች መጠቀም።

### ምህንድስና ንድፍ እና ሂደት

- በርካታ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሄዎችን መፍጠርና ማወዳደር።

- ተለዋዋጮች ቁጥጥር የሚደረግባቸው እና የመውደቅ ነጥቦች የአንድ ሞዴል ወይም የመጀመርያ ናሙና ገጽታዎች ለመለየት የሚታሰቡባቸው ፍትሃዊ ፈተናዎች ፕላን ማድረግና መፈፀም።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ጂዮግራፊ

- ቦታዎች ያሉበትን ለመለየት እና የነዚያን ቦታዎች ሰብኣዊና ፊዚካዊ ጠባዮች ለመግለፅ በጂዮግራፊካዊ መሳርያዎች መገልገል።
- በሜሪላንድ እና በዩናይትድ ስቴትስ የህዝብ እድገትን፣ ፍልሰትን፣ እና የሰፈራ ቅርፀቶችን መግለፅና መተንተን።
- ሰዎች ለምን እና እንዴት ከተፈጥሮአዊ አካባቢ ጋር እንደሚላመዱ እና እንደሚመች አድርገው እንደሚያሻሽሉ እና እነዚያ መለወጥ/ማሻሻል የሚያስከትሉ ተጽእኖዎችን አስረዳ/ጂ።

## የመረጃ/የኢንፎርሜሽን መሠረተ ትምህርት

- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ምንጮችን ያሉበትን ማወቅ፣ መምረጥ፣ እና መገምገም።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።
- መገናኛ አውታር ላይ ሰላማዊ ተግባሮችን ተጠቀም/ተጠቀሚ።

## ስነጥበብ

### ስነጥበብን መፍጠርና መገኖኘት

- የተለዩ ውጤቶችን ለማግኘት የስነጥበብን ንጥረነገሮችን በመምረጥና በመጠቀም በድርሰት ውስጥ በታዩ ሰዎች፣ እንስሳት፣ እና ነገሮች መካከል ግንኙነቶችን መወከል።
- በሚታየው ምላሽ ላይ የኪነጥበብ ስራዎችን ለመፍጠር፣ የስነጥበብ ክፍሎች፦ ቀለም/ከለር፣ መስመር፣ ቅርጽ፣ ለስላሳነት/ሻካራነት፣ቅርፅ፣ እሴት፣ እና ቦታ/ሥፍራ፣ እና የተመረጠው ንድፍ/ዲዛይን፦ ደርዝ፣ ድግግሞሹ፣ ንፅፅር፣ አወራረድ/እንቅስቃሴ፣ ማመጣጠን፣ እና በአንድነት/በህብረት ማደራጀት/ማዘጋጀት።

### ስነጥበብ አቀራረብና ዝንባሌ/ምላሽ

- ኣርቲስቶች ኣስተያየትንና ወቅታዊ ስሜትን በስነጥበብ የቃላት ዝርዝር በመጠቀም እንዴት እንደሚገናኙ ማወዳደርና መግለፅ።
- የተለያዩ እርቲስቶች ስለ ሰብኣዊ ተሞክሮ ሃሳቦቻቸውንና ስሜቶቻቸውን እንዴት እንደሚገልፁ ምርጥ የስነጥበብ ስራዎችን በመተንተን መግለጽ።
- ምርጥ የስነጥበብ ስራዎችን በዘውግ፣ ይዘት፣ ፎርም፣ እና በዘይቤ መመሳሰላቸውንና ልዩነታቸውን ለመወሰን ማወዳደር።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ መጫወት

- ሌሎች ተማሪዎች ሲዘምሩ ወይም የንጽጽር ክፍሎችን ሲጫወቱ ባለ ምት እና ሜሎዲያዊ ድግግሞሽ የበዛባቸው/ostinatos በትክክል ማቅረብ።
- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶችና የኣለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከኣጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ መዝሙሮችና ዳንሶች መጫወት።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- በሶልፌጅዮ ወይም በተመጣጣኝ ስርኣት በመጠቀም በትሬብል ስታፍ ላይ ቀላል የሙዚቃ ቃና ማንበብና ማቅረብ።

### የሙዚቃ ምላሽ/ዝንባሌ

- በተሰጠ የሙዚቃ ክፍል ውስጥ ተነፃፃሪ እና ተደጋጋሚ ሃረጎችን መለየት።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### ጤና-ኣራማጅ ኣካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ።

- በእርፍት የሚገኝ የልብ ትርታን፣ የልብ ትርታ ኣላማ፣ እና በጣም ከፍተኛ የልብ ትርታን ፍቺ መስጠት።
- የግለሰብ ጡንቻ ጥንካሬ እና የጡንቻ ቻይነት እና እንደሁኔታው መተጣጠፍ መርምር(ሪ) እና አወዳድር(ሪ)።

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች

- የራስ-በራስ-መገምገም እና ግብረመልስ በመንቀሳቀስ ክሂሎቶች መሻሻል ኣስፈላጊነታቸውን ማወቅ።
- በእጆችና በእግሮች መያዝና ማስተላለፍ ብቃት ማሳየት።

## የጤና ትምህርት

### የኣእምሮና የስሜት ጤንነት (MH)

- ውጤታማ የሆነ የግንኙነት/ኮሙኒኬሽን ችሎታዎችን በመለየት እውቅና ስጥ/ጪ።
- የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ደረጃዎችን መመርመር።

### ኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች እፆች/Alcohol, Tobacco, and Other Drugs (ATOD)

- የኣልኮል መጠቀም ኣካላዊ ውጤቶችን/ጉዳቶችን መለየትና ማገናዘብ/መመርመር።